የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሐምሌ. 22 ቀን 2002 ዓ.ም

## በአጭር መቀጨት ያለበት የወያኔ ሴራ

የወያኔ አገዛዝ ቀሰ በቀስ በባዕድ ሀገር ያለውን ሁኔታ በቁጥጥር ሥር አስገብቶ የተቃዋሚ ዜጎችን ድምፅ ለማፈን ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው። ይህም እርኩስ ተልዕኮ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተፋፋመ መጥቷልና ሁሉም ዜጋ ነቅቶ በመነሳት ሊያከሽፈውና በእንጭጩ ሊቀጨው ያስፈልጋል።

የወያኔ አገዛዝ ለዚሁ አፍራሽ ተልዕኮው ብዙ ሚሊዮን ብር የመደበ ሲሆን ብዙዎች ሰርጎገቦችና ሰላዮችን እንዲሁም አባሎቹን በስደተኛ ሽፋን ወደ አሜሪካና አውሮጳ ልኳል። ዛሬ እነዚህ ቅጥረኞቹን በመጠቀም በባዕድ ሀገሮች ያሉ የሃይማኖት ተቋማትንና ማህበራትን ለመያዝ ሰፊ ዘመቻ ከፍቷል። በመጪው ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓ.ም (ኦገስት 5/2010) በዋሺንግተን ዲሲ ወያኔን ደጋፊ ሰላማዊ ሰልፍ ማዘጋጀቱንም ሲገልፅ ለሀገር ተቆርቋሪ ለመምሰልና ለማዋናበድም የአባይን ጥያቄ ሊጠቀምም ተነስቷል። ለዚህ ሰልፍ የሚመጡትን የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች የመጓጓዣና የሆቴል የማረፊያ ወጪ የሚሸፍነውም የወያኔ ወዳጅ የሆነው ቱጃር የሳዉዲ አረብያ ዜጋ መሆኑም ተዘግቧል። ቀደም ሲልም ወያኔ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን (በኮሚቴ÷ በድረገፅ÷ በራዲዮ...ወዘተ ደረጃ) የልማትና እድገት ጥምረት በሚል ማደራጀቱም ተገልፆ ነበር። የሀገርን ሉዓላዊነት በሚፃረር መልክ ለግብፅ በባህር ዳር መሬት ያልሰጠ ይመስል ለሀገር ጥቅም በተለይ በአባይ ጉዳይ የቆመ አስመስሎ ሊያጨበረብር ይመኛል።

የወያኔን አገዛዝ ለዓለም ሕዝብ በማጋለጥ በባዕድ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ሚና የተጫወቱና ያላቸው ሲሆን ወያኔ ይህንን ለማክሸፍና የበላይነቱን ለማስረገጥ ሙሉ ትኩረት ሰጥቶና ጠላት ባላቸው ድርጅቶች ላይም የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍቶ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ይህ ሴራ በእንጭጩ ካልተመታ ጉዳቱ ቀላል ስለማይሆን ሁሉም ሀገር ወዳድ ይህን የወያኔ ጥረት ለማክሸፍ በጋራና በተጠናከረ መልክ ጊዜ ሳይሰጡ እንዲንቀሳቀሱ ኢሕአፓ ጥሪ ያስተላልፋል።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France